COVID@homeplus

# በኮቪድ አት ሆምፕላስ (COVID@HOMEPLUS) ውስጥ የታካሚ ህጻናትን የበሽታ ምልክቶች መከታተል

V1 9 ሰኔ/June 2022 ዓ.ም

ኮቪድ/COVID-19፤ ኢንፍሉዌንዛ እና ሌሎች የመተንፈሻ አካል በሽታዎች በሰዎች ላይ በተለያየ መንገድ ችግርን ይፈጥራሉ። ብዙ ሰዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ ህመም ይይዛቸው እና ወደ ሆስፒታል ሳይገቡ ያገግማሉ። ከህመሙ በሚያገግምበት ጊዜ የታማሚውን የበሽታ ምልክቶች መከታተል እና አስፈላጊ ከሆነ እርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ነው። የበሽታ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊካተት ይችላሉ:-

**አብዛኞች የተለመዱ የበሽታ ምልክቶች እንደ ጉንፋን ይመስላሉ፣ እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ:-**

- ትኩሳት
- የድካም መንፈስ
- መሳል
- የምግብ ፍላጎት ማጣት
- በአፍንጫ ፍሳሽ
- የጉሮሮ ህመም
- የማሽተት ወይም የጣእም ስሜት ማጣት ወይም መቀየር (ለኮቪድ/COVID-19 ታካሚዎች)
- መነጫነጭ

**ብዙ ያልተለመዱ የበሽታ ምልክቶች**

- የራስ ምታት
- በአፍ ለመመገብ  መቸገር እና መለስተኛ  ድርቀት
- የመተንፈስ ችግር
- ማስታወክ፣ ተቅማጥ

**ከባድ የበሽታ ምልክቶች**

- ለመተንፈስ ከባድ ጥረት ማድረግ፤ ለምሳሌ፡ ለፈጣን መተንፈስ ብዙ ጥረት ማድረግ ወይም በትንፋሾች መካከል ረዘም ላለ ጊዜ መቆም
- በጣም የማስተኛት፤ ለምሳሌ፡ ከእንቅልፍ ለመንቃት መቸገር ወይም መደናገር
- ከፍተኛ የድርቀት ችግር፤ ለምሳሌ፡ አነስተኛ የናፒ ጨርቅ እርጥበት ወይም ከመደበኛ ጊዜ ወደ ሽንት ቤት መሄድን መቀነስ፤ ወይም በጣም መጠማት
- የህመም ማስታገሻ መድሃኒት ከወሰዱ በኋላ የማይጠፋ ከባድ የደረት ወይም የሆድ እቃ ህመም
- ያለማቋረጥ የመደንዘዝ ስሜት ወይም የራስ ምታት
- ከአምስት ቀናት በላይ የሚቆይ ያለማቋረጥ ትኩሳት ወይም እድሜያቸው ከ3 ወራት በታች ለሆኑ ህጻናት ትኩሳት
- በእግሮች ላይ ህመም ወይም እብጠት መታየት።

ይህ የሁሉም የበሽታ ምልክቶች ዝርዝር አይደለም። እባክዎ ስላሳሰብዎት ሌላ ማንኛውም የበሽታ ምልክቶች ለመነጋገር ለኮቪድ አት ሆምፕላስ (COVID@homeplus) በቀጥታ መስመር በስልክ **1800 973 363** ይደውሉ።